# የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት

## የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

### የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የ2014 በጀት ዓመት ባቀረበው

### የ6 ወር የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የሰጠው

### ግብረ-መልስ

ጥር 2014

አዲስ አበባ

## መግቢያ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በህገ መንግሥቱ አንቀፅ 55 ንዑስ አንቀፅ 17 የህግ አስፈፃሚውን አካል አሰራር የመመርመር ስልጣን የተሰጠው ሲሆን በም/ቤቱ አሰራርና የአባላት ስነ ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 /በተሻሻለው/መሠረት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከሚከታተላቸው ተቋማት ውስጥ አንዱ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ነው። በመሆኑም የ2014 በጀት ዓመት የተቋሙን የግማሽ ዓመት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርትን በዝርዝር በማየት ጠንካራና ደካማ ጐኖችን በመለየት እንዲሁም ለቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በማካተት የሚከተለውን ግብረ መልስ ሰጥቷል።

## በጥንካሬ የተለዩ ጉዳዮች

1. ከሪፖርቱ ዝግጅት አኳያ ሪፖረቱ ዋና ዋና ማጠቃለያ/SUMMARY/ እና ቀጣይ ዝርዝር 12 የትኩረት አቅጣጫዎችን አካቶ የቀረበና ከጥራትም አኳያ ሲታይ ደረጃውን የጠበቀ ጥሩ የሪፖርት አቀራረብ መሆኑ፣
2. የኢንቨስትመንት አገልግሎት አሰጣት ማሻሻልን በሚመለከት የንግድ ሥራ ፈቃድ ማደስ አገልግሎት ከታቀደው እቅድ አንፃር ሲታይ በአጥጋቢ ሁኔታ ከእቅድ በላይ መከናወኑ፣
3. በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ውስጥ የኢንቨስትመንትና የቢዝነስ ከባቢ ሁኔታ (Ease of Doing Business) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ሃገራችን ያለችበትን ደረጃ እንዲሻሻል ለማድረግ 9 ተቋማትን ለማስተባበር እና ለመደገፍ ታቅዶ የሰባት ተቋማት የሪፎርም ስራዎችን በ" Ease of doing Business" ዙሪያ ክትትል እና ድጋፍ መደረጉ፣
4. በግብ1 ላይ በተደረጉ የኢንቨስትመንት ከባቢ ማሻሻያ ስራዎች ውስጥ አንዱ የሆነው የመሬት ምዝገባን በተመለከተ የመሬት ይዞታ ዲጂታላይዝድ በመደረጉ ለባለሀብቶች ብቻ የሚያገለገለግል የአንድ መስኮት አገልግሎት መሰጠት መጀመሩና ከዚህ ቀደም ለመሬት ምዝገባ መረጃ አገልግሎት የሚወስደውን ጊዜ በማሻሻል ከ52

ቀናት ወደ 7 ቀናት፣ የስም ዝውውር ከ30 ቀናት ወደ 2 ቀናት ዝቅ እንዲል መደረጉ፣

5. ከውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ ኮሚሽኑ የዓለም አቀፉ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ኤጀንሲ አሶሴሽን (WAIPA) እንዲሁም የዓለም ባንክ ግሩፕ በጥምረት የሚያዘጋጁትን አለማቀፋዊው የ 'Gold award 2021 ተሸላሚ መሆኑና የሀገራችን ኢንቨስትመንት ሴክተር እድገት፣ ዓለም አቀፋዊ እውቀና ማግኘቱና ተቋሙ በቀጣይ በአፈፃፀሙ ከዚህ በበለጠ ጠንክሮ እንዲሰራ የሞራል ማንቂያ ማግኘቱ፣
6. አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን በሚመለከት በይርጋለም የተቀናጀ ግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ያሉ 2 ድርጅቶች ምርታቸውን ለገበያ ለማቅረብ ከአርሶ አደሮች ጋር ቀጥታ ትስስር መፍጠራቸው። እነሱም Sunvado manufacturing Plc የተባለው ድርጅቱ ከ88 ሺህ አርሶ አደሮች ጋር እንዲሁም BM Avocado oil processing Plc ከአርባ ሺህ ገበሬዎች ጋር በቀጥታ ትስስር በመፍጠር ለአርሶ አደሮች የምርት ጥራት አጠባበቅና በመሳሰሉት ጉዳዩች ዙሪያ ከፍተኛ ስራ በመሰራት ላይ ያለ መሆኑና ማህበረሰቡ ከኢንዱስትሪ ፓርኮቹ በቀጥታ ተጠቃሚ እንዲሆን መደረጉ፤
7. በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ውስጥ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጪ ባሉ 59 ፕሮጀክቶች ወደ ማምረት ምእራፍ እንዲሻገሩ ለማድረግ ታቅዶ 78 ፕሮጀክቶች ወደ ማምረት እና አገልግሎት ለመስጠት /Operation/ ሲሸጋገሩ አፈጻጸሙም ከእቅድ በላይ በ133% ውጤታማ ክንውን መገኘቱ፣
8. በኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና በአካባቢው በሚገኙ የኢንቨስትመንት ድርጅቶች ላይ የደረሰውን ጉዳት አስመልክቶ ኮሚሽኑ ጉዳት ወደ ደረሰበት ስፍራ በመሄድ የመስክ ምልከታ በማድረግ በኢንዱስትሪ ፓርኩና በፓርኩ የሚገኙ ድርጅቶች ላይና ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጪ በሚገኙ ፕሮጀክቶች ላይ የደረሰውን አጠቃላይ ጉዳት በዝርዝር በማየትና በመገምገም በቀጣይ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹና ድርጅቶቹ ከጉዳቱ አገግመው ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቅንጅት በመስራት ፈጥነዉ ወደ ስራ እንዲገቡ የማበረታቻና ድጋፍ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ ኮሚሽኑ አጠቃላይ በፓርኩ ላይ የደረሰውን ውድመት በመተንተን የዳሰሳ ሪፖርት አዘጋጅቶ ማቅረቡ፣

9. በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት በአራቱም ፕሮግራሞች ያለው የፕሮግራሞች በጀት አፈጻጸም፣ የፊዚካልና ፋይናንሻል የፕሮግራም ውጤቶች አፈጻጸም፣ የውስጥና የውጪ ኦዲት ምርመራ ሂደት፣ ጊዜያዊ የፈሰስ ሂሣብ ቀጠራ ቁጥጥር እና ወርሃዊ የጥሬ ገንዘብና ሰነድ ቆጠራን በሚመለከት በሪፖርቱ እንደተመላከተው ውጤታማ የበጀት አጠቃቀምና የፋይናንስ አሰራር ለማጐልበት በግልፀኝነትና በጥራት ተሰርቶ መቅረቡና በኢንስቲትዩሽኑ ያለው የድጋፍ እና የክትትል ስራዎች የተጠናከሩ መሆናቸው፣

10. **ግብ6፦** ከኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኝ ኤክስፖርትን በሚመለከት ከሃምሌ እስከ ታህሳስ ወር የተከናወነውን የ6 ወር የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ስንመለከት ደ/ብርሃን፣ ድሬደዋ፣ ኢስተርን፣ ቦሌ ለሚና አይሲቲ ኢንዱስትሪ ፓርኮች በቅደም ተከተል የእቅድ አፈፃፀማቸው ከንውን /በዶላር\ ካቀዱት እቅድ በላይ መሆኑ፣

11. የፕሮጀክቶች ማህበራዊ ሃላፊነታቸውን ከመወጣት አኳያ ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ ካምፓኒ ሰበታ አካባቢ ባለው ፕሮጀክት ለአካባቢው ማህበረሰብ ትምህርት ቤት ገንብቶ ማስረከቡ፣ Kanoria Africa PLC እና Al-Asar PLC የተባሉ ድርጅቶች በቢሾፍቱና በዱከም አካባቢ ለአካባቢው ማህበረሰብ ነፃ የዉሃ አቅርቦትና ከሱማሌ ክልል ለተፈናቀሉ ዜጎች 12 ት/ቤቶችን መገንባታቸው፣ እንዲሁም (CICO) የሚባለው ድርጅት ደግሞ አማራ ክልል ለምዕራብ ጎጃም ዞን ቁጭ ለሚባል ከተማ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥገና ስራ ሰርቶ ለህብረተሰቡ ማስረከቡ፣

12. የኩነቶች (Events) ዝግጅትን በተመለከተ በግማሽ ዓመት ውስጥ 3 ኩነቶች በማዘጋጀት ባለሃብቶችን ለመመልመል ታቅዶ ከእቅድ በላይ 6 ኩነቶች የተዘጋጁ ሲሆን ከ30 ሀገራት የተለያዩ ኩባንያዎች ጋር የቨርችዋል ውይይቶችን በማድረግ ባለሃብቶችን የመመልመል እና የማግባባት(promotion) ስራዎች መሰራታቸው፣

## በዕጥረት የታዩ ጉዳዮች

1. የቀረበው የተቋሙ የግማሽ አመት ሪፖርት የክልሎችን የኢንቨስትመንት የሰራ አፈፃፀም ክንውን አካቶ የእቅዱ አካል አድረጎ አለማቅረቡ፣
2. ኮሚሽኑ ሁሉንም የኢንዱሰትሪ ፓረኮች ወደ ስራ ከማስገባትና እኩል ክትትልና ቁጥጥር ከማድረግ አኳያ ውስንነት መኖሩ፣ <u>ለአብነት</u> ሁዋጅያን(ለቡ)፣ ቬሎሲቲና ዲቢኤል ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣
3. ቡሬ አግሮ ፕሮሰሲንግና እና ባህዳር ኢንዱስትሪ ፓርኮች በግማሽ አመቱ ውስጥ ያከናወኑት የኤክስፖርት አፈፃፀም ካቀዱት እቅድ እና ከሌሎቹ የኢንዱስትሪ ፓርኮች አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ መሆኑ፣
4. የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በሚመለከት ምንም እንኳን ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ23 በመቶ ዕድገት ቢያሳይም በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ውስጥ ከታቀደው 2.13 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የተገኘው አፈፃፀም 1.64 ቢሊዮን ሲሆን ከታቀደው እቅድ አንፃር ሲታይ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑ፣
5. በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ውስጥ በአገራችን ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት አሳይተው ከተመለመሉ የውጭ ባለሃብቶች ውስጥ ለ125 ፕሮጀክቶች አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 75 ባለሃብቶች ብቻ አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጡ ሲሆን አፈፃፀሙ ከታቀደው እቅድ በታች መሆኑና ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ11 በመቶ ቅናሽ ማሳየቱ፣
6. በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ውስጥ 97 ፕሮጀክቶችን ወደ ትግበራ ለማሸጋገር ታቅዶ 69 ፕሮጀክቶች ማሸጋገር ቢቻልም ወደ ፓርኩ ውስጥ ገብተው የሚያለሙ ፕሮጀክቶች ከፓርክ ውጪ ከሚያለሙት ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ መሆኑና የፕሮጀክት አፈፃፀሙም ሲታይ የታቀደው ግብ ላይ አለመድረሱ፣
7. በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ምርት የወጪ ንግድ 139.4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 100.9 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲገኝ የእቅድ ክንውኑ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ16.6 በመቶ እድገት ቢያሳይም አፈፃፀሙ ግን ይደረስበታል ተብሎ ከታቀደው እቅድ በታች መፈፀሙ፣

8. እንደሚታወቀው ዋናው የፕሮጀክቶች አላማ ምርት ከማምረት ባሻገር ለዜጎች የስራ እድል መፍጠር ነው። ስለሆነም በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ውስጥ ህብረተሰቡ ከኢንቨስትመንት ተጠቃሚ እንዲሆን ለ71,361 ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ በግማሽ ዓመት ውስጥ ለ43,598 ዜጎች የስራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቢደረግም ከታቀደው እቅድ አንፃር ሲታይ ግን ከእቅድ በታች ዝቅተኛ ከመሆኑም ባሻገር በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተቀጥረው እየሰሩ ያሉ ሠራተኞች ጊዜአዊና ቋሚ መሆናቸው በቁጥር ተለይተው በሪፖርቱ አለመመላከቱ፣

9. በግማሽ ዓመቱ ውስጥ 120 የሚሆኑ የውጪ ሀገር ባለሞያዎችን በሀገር ውስጥ ባለሞያዎች ለመተካት ታቅዶ በስድስት ወራት ውስጥ በአምስት ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ 15 ባለሙያዎች ብቻ የተተኩ ሲሆን የተደረሰበት አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆኑ፤

10. የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና ምዝገባ አገልግሎቶች በዋናው መ/ቤት የተሰጡ የምዝገባ እና ሌሎች አገልግሎቶችን በሚመለከት፦ የማስፋፊያ ኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ አዲስ የንግድ ስም ጥያቄ በማጣራት ለመመዝገብ፣ የተለወጠ/የተሻሻለ ንግድ ምዝገባ ለማድረግ፣ ባለሀብቶች የሚያቀርቡትን የዋና ንግድ ምዝገባ ጥያቄዎችን አጣርቶ ለመመዝገብ ቢታቀድም የተፈፀሙትን ክንውኖች ስንመለከት የሁሉም ተግባራት አፈፃፀም በታቀደው እቅድ ልክ አለመፈፀማቸው፤

11. የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በተመለከተ በኢንዱስትሪ ፓርክ የማህበረሰብ ሬድዮ በመጠቀም ሠራተኛዉን የስራ ባህሉንና ምርታማነቱን እንዲያሳድግ ተከታታይ ፕሮግራሞችን ለማስተላለፍ ቢታቀድም አፈፃፀሙ በሪፖርቱ ውስጥ ተካቶ አለመቅረቡ፣

12. የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂን በሚመለከት በኢንዱስትሪ ፓርኮች አካባቢ የተፈጥሮ ሀብትንና የአካባቢ ጥበቃን ከመንከባከብ አኳያ ስራዎች ስለመሰራታቸው በሪፖርቱ አለመመላከቱ፣

13. የባለ ብዙ ዘርፍ አካታችነትን ከማሳደግ አኳያ የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፤ የወጣቶች፣ የህፃናት፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የአካባቢ

ጥበቃ ጉዳዮችን ለመተግበር፣ ለስርአተ ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት/Gender Responsive Budget/ እንደ አንድ የመንግስት ተቋም ትኩረት ተሰጥቶት ራሱን ችሎ በተቋሙ የተመደበ ባለመሆኑ ከሌሎቹ የበጀት ሥርዓቶች ጋር የሪፖርት ስራዎችን ለማከናወንና አጠቃላይ የተመደበውን በጀትና የወጪ አፈፃፀሙን መገምገም አለመቻሉ።

## በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

1. ሁሉም ፓርኮች በሙሉ አቅማቸው ወደ ስራ ገብተው ምርት ወደ ማምረት ደረጃ እንዲሸጋገሩ እንዲሁም ሌሎች ፕሮጀክቶች ወደ ፓርኩ ገብተው እንዲያመርቱ የሚመለከተው አካል በቀጣይ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ለአልሚዎቹ እገዛና ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
2. የኢንቨስትመንት ክላይሜት ሊያሻሽሉ የሚችሉ 1 ደንብና 3 መመሪያዎች፣ የማስፋፊያ መመሪያ ረቂቅ፣ እና የወጪ ንግድ ማበረታቻ እና የግብዓት ጥመርታ መመሪያዎች በሂደት ላይ ያሉ በመሆኑ ተዘጋጅተውና ፀድቀው በስራ ላይ እስከሚውሉ ድረስ አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ መደረግ ይኖርበታል፡፡
3. የኤክስፖርት አፈፃፀም ደረጃ ቁጥጥር የተደረገባቸው ድርጅቶችን በሚመለከት በኮሮናና በሌሎችም ምክንያቶች በ12 ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶች የኤክስፖርት አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ ደረጃ ያስመዘገቡ በመሆኑ በቀጣይ ድርጅቶቹ ያጋጠማቸውን ችግር በመፍታት የኤክስፖርት አፈፃፀማቸውን ከፍ ለማድረግ የሁሉም ርብርብና ጥረት ታክሎበት ድርጅቶቹ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ድጋፍና ክትትል መደረግ ይገባል፡፡
4. ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመከላከል ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ለመዘርጋት በታቀደው መሰረት በሁሉም የኢንዱስትሪ ፓርኮች ከጉሙሩክ ኮሚሽን፣ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን እና ከኮሚሽኑ ኮሚቴን በማዋቀር ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል እንዲረዳ የአሠራር ሥርዓት ጥናት የማድረግ ሥራ የተጀመረ ሲሆን በቀጣይ ጥናቱ አልቆ ወደ ትግበራ መግባት እንዲቻል ከወዲሁ የመረጃ ልውውጡና ክትትሉ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

5. የኢንፎርሜሽን ኮሙኑኬሽን ቴክኖሎጂን በተመለከተ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍና የመረጃ ፍሰቱን በCRM ቴክኖሎጂ ለማስተሳሰር፣ የኦላይን e-service አገልግሎት ከማሻሻልና እና የስራ ፈቃድ አገልግሎት በኦንላይን ከመስጠት አንጻር፡ የወጪና ገቢ ደብዳቤ (letter management) አሰራር ስርዓት ዘመናዊ እና ወጪ ቆጣቢ ከማድረግ አኳያ እንዲሁም የኮሚሽኑን የBusiness Email Licenseና Website Enhancement ወቅታዊና አለም አቀፍ ስታንዳርድ ያለው እንዲሆን ለማድረግ በኮሚሽኑ የተጀመሩትን ጥናቶችንና ጅምር ስራዎችን በማጠናቀቅ ወደ ስራ ለማስገባት እንዲቻል አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ መደረግ ይኖርበታል፡፡
6. አካባቢን ከብክለት ከመከላከል አንፃር በኢንዱስትሪ ፓርኮችና አምራች ድርጅቶች ውስጥ ተጠናቀው ያላለቁ የፍሳሽ ማስወገጃ ወይም ማጠሪያ ግንባታዎች በቶሎ ተጠናቀው ወደ ስራ እንዲገቡ ካልተደረገ በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩት ጉልህ ተፅእኖ ከፍተኛ በመሆኑ ከሌሎች ተባባሪ አካላት ጋር እና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በቅንጅት በመስራት ከወዲሁ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡
7. በአሸባሪው ህወሃት ጉዳት የደረሰባቸውን የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና በአካባቢው በሚገኙ የኢንቨስትመንት ድርጅቶች ላይ የደረሰውን ውድመት መልሶ ለማቋቋም እንዲቻል ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት አምራች ድርጅቶቹ ወደ ሙሉ አቀማቸው እንዲመለሱ የተጀመረው ድጋፍና ክትትሉ በቀጣይም ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡
8. ሀገራችን ከአጎዋ በመውጣቷ ወደ ውጪ ኤክስፖርት በሚደረጉ ምርቶች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድር በመሆኑ ከሌሎች አጋር ሀገሮች ጋር የተጀመሩና ወደፊት ሊጀመሩ የታቀዱ የንግድ ትስስሮች <u>**ለአብነት**</u> የአፍሪካ አህጉር ነፃ የንግድ ቀጠና/AFCFTA/፣ ከአውሮፓ ህብረት ጋር /EPA/፣ ከኤዢያ ሀገራትና ከመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ጋር ያለውን የንግድ ቀጠና ትስስር የበለጠ አጠናክሮ ለማስቀጠልና ሌሎች የገበያ አማራጮችን ለማስፋት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅርብ በመቀናጀት የሀገሪቷን ብሄራዊ ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ ክትትሉና የዲፕሎማሲው ስራ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።
9. በአንዳንድ የኢንዱስትሪ ፓርኮችና በፓርኮቹ ሼዶች ውስጥ የሚስተዋለውን የኤሌክትሪክ ሃይል አቀርቦት ችግር ለመፍታት ከሌሎች የኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር

በጋራ ተቀናጅቶ ያለውን የኤሌክትሪክ ሃይል በጋራ ለመጠቀምና ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ከኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እና ከሌሎችም ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ችግሮቹ መፍትሄ እንዲያገኙ የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ መደረግ ይኖርበታል።

10. ቅንጅታዊ አሰራርን በሚመለከት ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከሌሎች አቻ ከሆኑት ካምፓኒዎች ጋር በግብአት፣ በእውቀት ሽግግርና በሌሎችም እንዲሁም ከሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅተው በሚሰሩበት ጉዳይ ላይ አብሮ በመስራት ግንኙነታቸውን አጠናክው መቀጠል ይኖርባቸዋል።
11. የኢንቨስትመንት ኮሚሽን የክልሎችን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በአግባቡ ክትትልና ድጋፍ ከማድረግ አኳያ ክፍተት ስላለ በቀጣይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል።
12. በኢንቨስትመንት የተፈናቀሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች መለሶ ከማቋቋም አንፃር ኢንቨስትመንት ኮሚሽኑ ኃላፊነቱን ወስዶ የበኩሉን ማድረግ ይኖርበታል።
13. ፕሮጀክቶች ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ከመወጣት አኳያ እያደረጉ ያለውን አስተዋፅኦ በጠንካራ ጎኑ የተቀመጠ ሲሆን በቀጣይ ግን በሁሉም ፕሮጀክቶች ተፈፃሚነት እንዲኖረው ኢንቨስትመንት ኮሚሽኑ በትኩረት እንዲከታተለው ይደረግ።

## ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በ2014 በጀት አመት በሁለተኛ ሩብ ዓመት በዕቅድ የያዛቸውን ተግባራት ለማከናወን የኮሮና ወረርሽኝን፣ በአሸባሪው ህወሃት የተቀሰቀሰው የሰሜኑን ጦርነትና ከዚያ ጋር በተያያዘ የውጪ ሚዲያዎች የሚያሰራጩትን የተዛባ መረጃ ተቋቁሞ በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ያቀዳቸውን ተግባራት በአብዛኛው በእቅዱና እንዳንዶቹንም ከእቅድ በላይ ማከናውን ችሏል፡፡ ስለሆነም በቀሪዎቹ ወራቶች በጥንካሬ የተሰጠውን አስተያየት አጠናክሮ በማስቀጠል ሌሎች በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲተገበሩ በግብረ መልሱ የተመላከቱትን ጉዳዮች ትኩረት ሰጥቶ መሠራት እንዳለበት ኮሚቴው እቅዱን በመገምገም ይህን አስተያየት ሰጥቷል፡፡